# የጠርሙስ ውሃ

By: cosmos-2000, Mar 2009

40 ዓመት ሙሉ ባገራችን
ፈውስ አላገኘም በሽታችን::
ስላልዘነበ አጥግቦ
በሽታ ገባ ተስቦ::
ባይተሻሹ ሄደው
ይቀር ነበር በዛው::

እንደሚገባ ያወቁቱ
እጅግ በጣም ጥቂቱ
ቆርጠው ጠበቁት
ያገረሰብ መድኀኒት::
መድኀኒቱን ያላዘዙ
ሲጠራጠሩ ተያዙ::

እነሆ ታውቋል መነሻው
ያገሬ ሰው ሚጠጣው
ተበክሎ ነው ዉሃው::

ከላይ ከራሱ ካልጠራ
መታመም አይቀር በተራ::
ዶፍ ቢወርድ ባገሪቱ
ይጠርገው ነበር ካናቱ::

ማለቃችንን የፈለጉ
ወደ ውጭ ላኩት እያሸጉ::
ጠላቶቻችን ሲልኩት
ሴቶች አዘዙ ቦይኮት::
በሽታ ይጠፋል ካገሩ
ሴቶች መታገል ሲጀምሩ::

ውሃ ስትቀዱ በጋን
ተሎ አትጠጡት ይስከን::
የጠርሙሱ ውሃ አለው ቆሻሻ
እነሆ ዘግቧል ከመጨረሻ::

እየታመመ ነው ሃገሩ
ተወግቶ ይውጣ ከሥሩ::

አንድ ላይ ይሁን ቆሻሻው
አግድሞ እንዳይፈስ እንዳሻው::
መጠንቀቅ ያሻል በጣም
እየበነነ እንዳያሳም
ይቃጠል ካላችሁ መልካም::

ማለፉ አይቀር አሰቃይቶ
እንዳይመጣ አረሳስቶ
መክተብ ነዋ አደራጅቶ
እንዲመክት ለይቶ::

ማሰብ ያለብን አሁን
እንዳይተካ ድቅል ጂን
ግንቦት ያበቀለብን::

ዘረኝነትን የሚያጎላ
ሴራ እንዳይኖር በስተኋላ
ለመፍትሄው አምጡ መላ::
የጠርሙስ ውሃ ስታነሱ
የኔን ምክር አትርሱ::

ትልቁ መፍትሔ ላገር
ያረጀው መሣሪያና መስመር
ከግር እስከ ራሱ ሲቀየር::
ቀላል አይደለም ሥራው
አንድ ሆነን ካልያዝነው::

ንጽሕና የለም ወንፊት አልባ
በርከን በርከኑ የሚገባ
ተውሳካት ሳይቀር ተስቦ
አንቆ የሚያስቀር ሰብስቦ::

ሁሉም ንጹሕ ነው ባንል
መች ይጠፋል ጋኔል
እንዳንፈወስ ሚከጅል::
ወንፊታችንን የሚነድል
ይኸው እያየን አይደል::

ለጤናችን ማስተማመኛ
የነቃ የታጠቀ ዘበኛ
ይመለመላል ከኛ

አሰልጣኞቹ እኛ
ተጠያቂነቱ ለኛ::

ብንተማመን ለእራሳችን
ምንከባባር በወጋችን
ምንተዛዘን በእምነታችን
ማን ይሆናል እንደእኛ
ሙሉ በሙሉ ጤነኛ::